# የ ቦንድ የጥቃት ጥበቃ

*ይህ ትርጉም በSocial Development Direct እና በTranslators Without Borders ለማሳወቅ ብቻ ታስቦ የተሰራ ነው። ትክክለኛነቱን BOND ማረጋገጥ አይችልም። ብቸኛው ኦፊሴላዊ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተጻፈ ሲሆን በBOND* [Safeguarding policy templates | Bond](#) *[ድረገጽ ላይ ይገኛል]፤*

# የሥነ-ምግባር ደንብ

## መግቢያ

ራእይና እሴቶቹን ለማስቀጠል [መንግስታዊ ያልሆነው ድርጅት] የሠራተኞቹን እና ተያያዥ ሰዎችን የሥነ-ምግባር ጠባይ በከፍተኛ ደረጃ ለመያዝ ቁርጠኛ ነው። ተግባቦትን ለመጨመር ይህ የሥነ-ምግባር ቁልፍ ዘርፎች መመርያ [መንግስታዊ ያልሆነው ድርጅት] ከሠራተኞች የሚጠብቀውን ይዘረዝራል።

## ወሰን እና ዓላማ

ይህ የሥነ-ምግባር መመርያ በሁሉም ዓለም አቀፋዊ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] እና የሀገር ውስጥ ተቀጣሪ ሠራተኞች ላይ ተግባራዊ ነው። የተወሰዱት የሥነ-ምግባር መመርያዎች ለሁሉም በጎ ፈቃደኞች፣ አጋሮች፣ ሠራተኞችና ተቋራጮች ይሰራል።

የዚህ የሥነ-ምግባር መመርያ ዓላማ ለ[መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ከሚሰሩ ሠራተኞች የሚጠበቀውን ሥነ-ምግባር ለመወሰን ሲሆን ይህ የሁሉም የሥራ ቅጥር ውሎች አካል ነው። መመርያው በማንኛውም ጊዜ ይተገበራል። የሥነ-ምግባር መመርያውን መጣስ ለእርምት እርምጃ እንደ መነሻ ሲሆን ከሥራ ገበታ እስከማባረር ያደርሳል።

የሀገር ውስጥ ሕጎች እና ባህሎች በበቂ መጠን በአንዱ ሀገር ከሌላው እንደሚለያይ ከግምት ቢገባም [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ዓለም አቀፋዊ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፤ ስለዚህ የሥነ-ምግባር መመርያው የተዘጋጀው ከዓለም አቀፍ እና የተባበሩት መንግስታት ደረጃዎች ነው። [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ሠራተኞች በሚሰሩበት የትኛውም ቦታ የአካባቢውን ሕግ በጣም የከረረ ካልሆነ ማክበር አለባቸው፡፡ የከረረ ከሆነም መመርያው ተግባራዊ ይሆናል።

## ራእይና እሴቶች

[የመንግስታዊ ያልሆነ ድርጅቱን ዝርዝር ተልእኮዎች እና ተቋማዊ እሴቶች ያስገቡ]

## የሥነ-ምግባር መመርያ ደረጃዎች

እንደ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ሠራተኛ እኔ:

**የ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ታማኝነት እና ዝናን ለመጠበቅ የራሴን ሙያዊ እና ግላዊ ሥነ-ምግባር ከ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] እሴቶች እና ደረጃዎች ጋር መስማማቱን አረጋግጣለሁ፡፡**

- ሁሉንም ሰዎች በፍትሃዊነት በአክብሮት እና በክብር አገለግላለሁ
- [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት]ን በመወከል በዓለም አቀፋዊ አውድ ውስጥ ስሰራ ወይንም ዓለም አቀፋዊ ጉዞ ሲደረግ የአካባቢውን ሁሉንም ሕጎች አከብራለሁ ለአካባቢው ባህልም ጥንቁቅ እሆናለው፡፡
- ሥነ-ምግባሬ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት]ን ወደ አለመግባባት የሚከት አለመሆኑን እና የተቀጠርኩበትን የሥራ ድርሻ የመስራት ችሎታዬ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ወይም የሚቀንስ እንዳይሆን እተጋለሁ፡፡
- በአልኮል ተፅእኖ ውስጥ ሆኜ ወይንም ይዤ፤ ወይንም ደግሞ አደንዛዥ እፅ በ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ቅጥር ውስጥ እና መኖርያ አካባቢ ይዤ አልገኝም

**ጥቃታዊና በዝባዥ ባህሪ ላይ አልሳተፍም**

- ከህጻናት(እድሚያቸው ከ 18 ዓመት በታች ከሆኑ ሰዎች) ጋር ወሲባዊ ድርጊት አልፈጽምም፡፡ ስለ ዕድሜው/ዋ የተሳሳተ ግምት መያዝ መከላከያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡
- ወሲብን በ ገንዘብ፣ በሥራ፣ በአገልግሎቶችና ቁሳቁስ አልቀይርም፤ እንዲሁም ወሲባዊ ችሮታዎችን ወይንም አስነዋሪ፣አዋራጅና በዝባዥ ባህሪያት የተከለከሉ መሆናቸውን አውቃለሁ። ይህ ለተጠቃሚዎች በልውውጥ የሚደረግን ማንኛውንም ድጋፍ ይመለከታል።
- በማይመጣጠን የአቅም ልዩነት ላይ ከሚገኙ እና ከእገዛ ተጠቃሚዎች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት አይኖረኝም፡፡
- ከህጻናትም ሆነ ከተጋላጭ ሠዎች ጋር የህጻናት ጉልበት ብዝበዛን እና ዝውውርን ጨምሮ የገንዘብ ብዝበዛን የሚያደርሱ እንቅስቃሴዎች ላይ አልሳተፍም፡፡
- ህጻናትም ላይ ሆነ ተጋላጭ አዋቂ ላይ አካላዊ ጥቃት አላደርስም፡፡
- ህጻናትም ላይ ሆነ ተጋላጭ አዋቂ ላይ መንፈሳዊም ሆነ ሳይኮሎጂያዊ ጥቃት አላደርስም፡፡

**የሁሉንም [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ሠራተኞችን እና ተያያዥ ግለሰቦችን (በጎ ፈቃደኞች፣ አጋሮች፣ አቅራቢዎች እና ተቋራጮች) ደህንነት፣ ጤና እና በጎ መሆን አረጋግጣለሁ**

- ህጋዊና ድርጅታዊ የደህንነት መስፈርቶችን በስራ ስፍራዬ ላይ እተገብራለው
- ማንኛውንም የአካባቢውን የደህንነት መመርያዎች በመተግበር አስፈላጊ ለውጦች ሲኖሩ አመራሩን በማሳወቅ በንቃት እሳተፋለሁ
- አጋር ድርጅቶችን እና አብረናቸው የምንሰራቸውን ማኀበረሰቦች ጨምሮ የእኔንም ሆነ የሌሎች ደህንነት፣ ጤና እና በጎ መሆን ላይ አላስፈላጊ አደጋ ሊያስከትል በማይችል ባህሪ እንቀሳቀሳለሁ፡፡

**በ[መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ተቀጥሬ በሥራዬ ምክንያት ለማገኛቸው መረጃዎች፥ ሃብቶችና ግብአቶች ሃላፊነት እወስዳለሁ፡፡**

- በ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] የተሰጠኝን ገንዘብንና ንብረትን ጨምሮ ሀብትና ግብአት በሀላፊነት እጠቀማለሁ፡፡
- የ[መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት]ን የመረጃ ቴክኖሎጂ (IT) እቃዎችን፣ ሶፍትዌሮችን ወይም ኢሜይል እና ማኀበራዊ ሚድያን በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ህግ ተቀባይነት በሌለው እንቅስቃሴ እና የወንጀል ጥፋትን በሚያመጣ ምግባር መልኩ አልጠቀምም። ይህም በጥብቅ መገለጫዎች ወይም ፅንፈኝነትን በሚያበረታታ መልኩ ማንኛውንም ቡድንን የሚያስፈራራ ወይም የሚተነኩስ መረጃን ይጨምራል፡፡

- የ[መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት]ን የመረጃ ቴክኖሎጂ (IT) መሳርያን አላስፈላጊ ነገሮችን እና ጥቃታዊ መረጃዎችን ለማየት ማለትም ወሲባዊ ይዘቶችን (ፖርኖግራፊ) ወይንም የህጻናት ብዝበዛን ጨምሮ (በእነዚህ ብቻ ሳይገደብ) ለማየት፥ለማውረድ፥ ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት አልጠቀምም፡፡

**የግል ህይወቴና ባህሪዬ ከሃላፊነቴ ጋር የጥቅም ግጭት በማያመጣ መልኩ ሥራዬን እሰራለሁ**

- ማንኛውንም የገንዘብ፣ የግልም ሆነ የቤተሰብ (ቅርብ ጓደኝት) ለሥራ ጉዳይ እና በ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ሥራ ላይ ተጽእኖ የሚያመጣ ከሆነ አሳውቃለሁ፡፡
- ለቁሳቁስና አገልግሎት ጥቅማጥቅሞችንና ውሎችን ወይንም በ[መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ውስጥ ለስራና እድገት ፥ ለማንኛውም የገንዘብ የግል እና የቤተሰብ (ጥብቅ ጓድኝት) ፍላጎት ላለኝ ሰው በመስጠት አልሳተፍም፡፡
- ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ተመራጭ ወይንም ለሌላ ግልጽ ድርሻ ለመመረጥ ከመስማማቴ በፊት ከ[መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ፍቃድ እጠይቃለሁ
- ትልልቅ ስጦታዎችንም ሆነ አበል (ማበረታቻዎችን) ከመንግስት፣ ከምሰራበት ማኅበረሰብ፣ ከለጋሾች፣ ከአቅራቢዎች እና በ[መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ተቅጥሬ በመስራቴ ከሚሰጡኝ ሰዎች አልቀበልም፡፡

**ምስጢራዊነትን መጠበቅ**

- ለይፋዊ የሥራ ጉዳዮች ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጋለሁ፤ እንዲሁም ከባልደረቦቼ እና ከሥራ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ወይንም ጥብቅ ምስጥራዊ መረጃን በህግ ካልተጠየቅኩ በስተቀር አላወጣም፡፡

# ቅሬታዎች እና ሪፖርቶች

የ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ሠራተኞች ያዩትን፣ ያወቁትን ወይም የጠረጠሩትን አደጋ፣ ብዝበዛም ሆነ የተሰማቸውንና የተነገራቸውን ወይንም ከሥነ-ምግባር ደንብ ድንጋጌዎች የወጣና ነገር ካለ ጉዳዩን ወደ ተገቢው ሥራ አስኪያጅ ማቅረብ አለባቸው፡፡ በ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] ስጋቶችን የሚያቀርቡ ሠራተኞች በ የስራ ቦታ ብልሹ አሰራር ማሳወቂያ ፖሊሲ ይጠበቃሉ።

ሠራተኞች በደንብ ጥሰት ዙርያ ቅሬታ ወይንም ስጋት በፍጥነት ለቅርብ አለቃቸው ማሳወቅ አለባቸው። ሠራተኛው ለቅርብ አለቃው ለማሳወቅ ምቾት ካልሰጠው(ለምሳሌ ሪፖርቱ ትኩረት አይሰጠውም ብሎ ካሰበ ወይንም ያ ሰው በሪፖርቱ ውስጥ ከተጠቀሰ) ለሌላ ተገቢ የስራ ባልደረባ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡ ለምሳሌ ይህ የበላይ ሥራ አስኪያጅ ወይንም ለ ሰው ሃይል ቡድን አባል ይሆናል።

በ [መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት] የቅሬታ ፖሊሲና አሰራር መሰረት ሪፖርቶችን ወይንም ቅሬታዎችን የሚቀበሉ ሠራተኞች በፍጥነት እርምጃ መውሰድ ወይንም ማስተላለፍ አለባቸው

# ተያያዥ ፖሊሲዎች

የቅሬታዎች ፖሊሲዎች እና አካሄዶች

በሥራ ቦታ የጤና እና ደህንነት ፖሊሲ

በሥራ ቦታ ብልሹ አሰራርን የማሳወቅ ፖሊሲ

የማጭበርበር እና ሙስና ፖሊሲ

የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ

ፀረ-ማንጓጠጥ እና መተንኮስ ፖሊሲ

የደህንነት ፖሊሲ

የ መረጃ ቴክኖሎጂ (IT) አጠቃቀም ፖሊሲ

______________________________________________________________________

ምደባዬን ስቀበል ባህሪዬን በደንቡ መስፈርቶች መሠረት ሃላፊነቴን እወጣለሁ

ስም፡

ፊርማ፡

ቀን: